# አንጾኪያ ኢንተርናሽናል ሕብረት
Antioch International Fellowship
821 South Midvale Blvd.
Madison, Wisconsin 53711


## የተቀደሰ ጉባኤ – በማዲሰን ከተማ
Saturday, February 2, 2008 (2:00 – 6:00 pm)

*ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፤ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤*
*እርሱ መንገዱን ያስተምረናል። ኑ፤ በእግዚአብሔር ብርሃን እንመላለስ። (ኢሳ 2)*

በማዲሰን ከተማና በጎረቤት አውራጃዎች ለምትገኙ ወገኖቻችን ሁሉ፦

በመጀመርያ፤ እኛ የአንጾኪያ ኢንተርናሽናል ወንጌላዊት ቤተ ክርስትያን አባሎች፤ ለጌታችንና መድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልና ለ2008 የምሕረት ዓመት፤ እግዚአብሔር አምላካችን፤ እንኳን በሰላም አደራሳችሁ በማለት፤ የጠበቀና የከበረ ሰላምታችንን እናቀርባለን። አዲሱ ዓመት፤ ከእግዚአብሔር ብቻ የሚገኝ፤ የምሕረት፤ የአምልኮና የቅድስና፤ የፍቅርና የሰለም፤ የበረከትና፤ የተትረፈረፈ የምስጋና ዓመት እንዲሆንላችሁ፤ ከልብ የመነጨ ጸሎታችንና ምኞታችን ነው።

"*እናንተ በአምላክ ፊት የምታገለግሉ፤ የተቀደሰ ጉባኤ ጥሩ*" በሚል በእግዚአብሔር ቃል አሳሳቢነት መሰረት (*ኢዩኤል 1፡14*)፤ አዲሱን ዓመት፤ ለእግዚአብሔር ምስጋናን በማቅረብ፤ በመዝሙርና በጸሎት፤ በእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና አምልኮ፤ በኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ የእራት ግብዣ፤ የተቀደስና የተባረከ ጊዜ ከኛ ጋር እንድታሳልፉ በአክብሮት እንጋብዛለን።

ቤተ ክርስትያናችን፤ ከመሃል ከተማው (downtown Madison) በስተ መዕራብ በኩል የምትገኝ ስትሆን፤ ከተማውን ከሚዞር Beltline መውጫ በ 0.8 mile ርቀት ትገኛለች። አቅጣጫውን ከዚህ website (http://www.midvalebaptist.org/directions.html) ማግኘት ይቻላል።

ፕሮግራማችን ቅዳሜ February 2, 2008 ከሰዓት በኃላ በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር በስምንት (8) ሰዓት (2 pm) ይጀመራል። የፕሮግራማችን አጀንዳች እንደሚከተለው ነው፦

| በኢትዮጵያ አቆጣጠር | በፈረንጅ አቆጣጠር | የፕሮግራም ይዘት |
|---|---|---|
| 8 ሰዓት | 2፡00 pm | እንኳን ደህና መጣችሁ |
| 8፡10 | 2፡10 pm | መዝሙሮች |
| 8፡30 | 2፡30 pm | የምስክርነትና ይምስጋና ጊዜ |
| 9 ሰዓት | 3፡00 pm | የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና አምልኮ |
| 9፡30 | 3፡30 pm | የ Chicago መዘምራን (choir) |
| 10 ሰዓት | 4፡00 pm | የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት (ክፍል 1) |
| 10፡45 | 4፡45 pm | መዝሙርና ጸሎትስ |
| 11 ሰዓት | 5፡00 pm | የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት (ክፍል 2) |
| 11፡45 | 5፡45 pm | የወንጌል ጥሪ |
| 12 ሰዓት | 6፡00 pm | ራት ይቀርባል |

ወገኖቻችን ሆይ፦ ጥሪያችንን በማክበር የፕሮግራማችን ታካፋዮች እንደምትሆኑ ባለ ሙሉ ተስፋዎች ነን። እኛ በእናንተ መገኘት እንደምንባረክ ሁሉ፤ እናንተም በዝግጅታችን ተበርካችሁ እንደምትሄዱ እርግጠኞች ነን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

ለተጨማሪ ኢንፎርሜሽን፤ በሚከተሉት የስልክ ቁጥሮች ይደወሉ (መለእክት ይተዉ)።
1. 608-273-2616 (ኃይለ በርሀ)
2. 608-827-0036 (በቀለ ኃይለሥላሴ)